Advanced Journal of Interdisciplinary Studies
Volume 10, Issue 1, 2026 | Pages 2889–2902
Journal homepage: www.ajids.dmu.edu.et

Research Article

አማርኛን እንደ አፍ መፍቻ እና እንደሁለተኛ ቋንቋ ለማስተማር ለ5ኛ እና ለ6ኛ ክፍል በተዘጋጁት መፃህፍት ውስጥ የቀረቡት ሰዋስዋዊ ይዘቶች ትክክለኛነት[1]

The accuracy of the grammatical content presented in the textbooks prepared for teaching Amharic as a mother tongue and as a second language for Grades 5 and 6.

አለማየሁ ተመስገን[1]

[1]በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ-አማርኛ ትምህርት ክፍል፣ ደብረ ማረቆስ ዩኒቨርሲቲ፣ ፖ.ሳ.ቁ. 269፣ ደብረ ማረቆስ፣ ኢትዮጵያ

ARTICLE INFO

Received: 6 July 2025
Revised: 25 February 2026
Accepted: 15 March 2026
Available online: 15 September 2026

KEYWORDS/ ቁልፍ ቃላት

ሰዋስው፣
የሰዋስው ትክክለኛነት፣
ቅርፅ ተኮር ዘዴ፣
ፍች ተኮር ዘዴ ፣

አህፅሮተ ጥናት /ABSTRACT

የዚህ ጥናት ዓላማ አማርኛ ቋንቋን እንደ አፍ መፍቻና እንደሁለተኛ ቋንቋ ለሚማሩ ለ5ኛ እና ለ6ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማራ፣ በደቡብ፣ በኦሮምያና በአዲስ አበባ መስተዳድር ትምህርት ቢሮዎች በተዘጋጁት መጻሕፍት ውስጥ የቀረቡትን የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች (ስነምዕላድ/ቃል፣ ሀረግና ዓረፍተ ነገር) ትክክለኛነት መገምገም ነው። መረጃዎች የተሰበሰቡት በሰነድ ፍተሻ ሲሆን በክልሎች፣ በከተማ አስተዳድር ትምህርት ቢሮዎችና በትምህርት ሚኒስቴር ለተጠቀሱት የክፍል ደረጃዎች (ለ5ኛ እና ለ6ኛ ክፍል) ከተዘጋጁት መማሪያ መጻሕፍትና የመምህር መምሪያ ነው። የተገኙት መረጃዎች በገላጭ የምርምር ስልት የተተነተኑ ሲሆን በምዕላድ/ቃል፣ ሀረግና ዓረፍተ ነገር በሚሉ ንዑስ ርዕሶች ቅደም ተከተል ተደራጅተው ቀርበዋል። የተገኙ ውጤቶች እንደሚያሳዩትም የተወሰኑ ይዘቶች የቋንቋውን ሥርዓት ጠብቀው የቀረቡ ሲሆን አብዛኛዎቹ የሰዋስው ይዘቶች ግን የቋንቋውን ሰዋስዋዊ ትክክለኛነት ያልጠበቁ ናቸው። ከታዩ ችግሮች ውስጥ በዋናነት ምዕላድና ተውሳከ ግስ በሚለው የቃል ክፍል ሥር የቀረቡት ማብራሪያዎችና ጥያቄዎች ተጠቃሽ ናቸው። ከዚህ በመነሳት ለወደፊት የታዩ ችግሮችን ለመቅረፍ ያስችላሉ የተባሉ ንድፈ ሃሳባዊና ሥነ ትምህርታዊ አስተያየቶችን በመስጠት ጥናቱ ተጠናቋል።

The purpose of this study is to evaluate the accuracy of the grammar content (Morpheme/words, phrases and sentences) provided in the books prepared by Amhara, South, Oromia and Addis Ababa government education offices for 5th and 6th grade students who learn Amharic as a mother tongue and as a second language. Data were collected through document inspection and from the textbooks and teacher's guide prepared by the states, city government education offices and the Ministry of Education for the specified grade levels (5th and 6th grade). The obtained data were analyzed by descriptive research method and were organized in the order of sub-themes such as Morphemes/words, phrases and sentences. The results show that certain contents are presented in the correct language system, but most of the grammatical contents are not presented in the grammatical accuracy of the language. Among the problems that have been observed, mainly the explanations and questions presented under the Morpheme and Adverb sections are mentioned. Based on this, the research is concluded by giving theoretical and practical suggestions that will help to solve the problems.

1የሰዋስው ትክክለኛነት የሚለው ቃል በ Juzek, T.S. (2016) “Grammatical Correctness” በሚል የቀረበውን ቃል ተክቶ የገባ ነው።

Corresponding author: Alemayehu_temesgen@dmu.edu.et / haddisalex@gmail.com (ተመስገን አ.)

DOI: http://doi.org/10.20372/ajids.2026.2889

1. መግቢያ

1.1. የጥናቱ ዳራ

የሰዋስው ምንነትን በተመለከተ የዘርፉ ምሁራን እንደሚከተለው ሲበይኑት ይስተዋላል፡፡ ኡር (1991፣86) "ቃላት አንድ ላይ በመሆን ትክክለኛ ዓረፍተ ነገር የሚመሠርቱበት መንገድ ሰዋሰው ይባላል" ይላሉ፡፡ ኬክና ኪም (2014፣33) ደግሞ "ሰዋስው ማለት ቃላትና ምዕላዶች አንድ ላይ በመጣመር ዓረፍተ ነገር የሚመሰርቱበት ሥርዓት ወይም ሕግ ማለት ነው" ካሉ በኋላ ውስብስብ የሆነው ጉዳይ ግን የሰዋስው ገለጻ ከዓረፍተ ነገር በላይ ነው ወይ? የሚለው ጉዳይ ነው ይላሉ፡፡ ሀርመር (1987፣1) በበኩላቸው "ቃላት በዓረፍነገር ምስረታ ሂደት አንድ ላይ የሚደራጁበት ሥርዓት ነው" ይላሉ፡፡ በማያያዝም ቃላት በብዙ ቁጥር፣ በአፍራሽ ወይም በጥያቄ ጊዜ የሚመሠርቱትን መዋቅር ወይም ሁለት ሀረጎችን በምናያይዝበት ጊዜ ያለው የቃላት ቅደም ተከተል ሰዋስው ተብሎ እንደሚጠራ ይገልፃሉ፡፡

ኮልማንና ክላፐር (2005፣68) እንደሚሉት ደግሞ ተግባራዊ ሥነልሳን ሰዋስውን ቀጥተኛ እና ኢ-ቀጥተኛ የሆነ እውቀት በማለት በሁለት ይከፍሉታል፡፡ ኢ-ቀጥተኛ የሰዋስው እውቀት ማለት ተጠቃሚው አንድ የሆነ ቅርፅ ለምን ትክክል እንደሆነ ሳያውቅ በፍጥነት አገልግሎት ላይ የሚያውልበትን መንገድ የሚያመለክት ሲሆን ይህን የሰዋስው እውቀት በቀጥታ ወይም በፍጥነት በማስተማር ተፅዕኖ ማሳደር እንደማይቻል በሁለተኛ ቋንቋ ለመዳ ላይ ጥናት ካደረጉት ተመራማሪዎች ውስጥ ኤሊስ (1990)ን በመጥቀስ ያስረዳሉ፡፡ ቀጥተኛ እውቀት ግን ስለ ሰዋስው ያለ እውቀት ነው፡፡ ይኸውም የቋንቋ አፍልቆታችንን ትክክለኛነት የምናረጋግጥበት ወይም የጽሑፍ ቋንቋችንን የምንፈትሽበት ሲሆን አርትኦት በሌለበት የቋንቋ አጠቃቀም ውስጥ በፍጥነት አገልግሎት የማይሰጥ ነገር ግን ሆን ተብሎና በዝግታ በውጭ ቋንቋ ወይም በአፈ-ፈቶች ላይም ቢሆን ዘገባ በሚፅፉበት ጊዜ አገልግሎት ላይ የሚውል የእውቀት ዓይነት ነው፡፡ ኤሊስ (2002ለ)ን በመጥቀስ እንደሚያስረዱት ቀጥተኛ እውቀት የኢ-ቀጥተኛ እውቀት ለመዳ ሂደትን ማገዝ ይችላል፡፡ በዚህ ምክንያት የሰዋስው ማስተማር ትኩረት ማድረግ ያለበት የተማሪዎችን ቀጥተኛ እውቀት በማዳበር ላይ ነው ይላሉ፡፡

የቋንቋውን መምህር ለማሰልጠን፣ መማሪያ መጻሕፍትን ለማዘጋጀትና የይዘቶችን ቅደም ተከተል ለመወሰን ወዘተ የሰዋስው አስፈላጊነት አከራካሪ አይደለም፡፡ ለዚህም ነው ኮልማንና ክላፐር (2005፣73) ሰዋስዋዊ መዋቅርን በቁጥጥራዊ ልምምድ (Controlled Practice) ውስጥ ማስተማር ብዙ ጥቅሞች አሉት፡፡ ከእነዚህም ውስጥ ተማሪዎች እርስ በእርስ በመረዳዳት ተጨማሪ ግብዓትን ያገኛሉ፤ በተደጋጋሚ የሚቀርበው መዋቅር ቁልፍ የሆኑ ሥነልሳናዊ ባሕርያትን ለመረዳት የሚያስችሉ እድሎችን ያቀርባል፤ ተማሪዎች በተለይም በጽሕፈት ልምምድ ጊዜ የራሳቸውን አፍልቆት በጥንቃቄና ሆነ ብለው ለማረም ያስችላቸዋል፡፡ ስለ ሰዋስው ያለንን ግልፅ እውቀት ይጨምርልናል፡፡ ይህም የቋንቋውን ሕግ ትክክለኛ እና ፈጣን በሆነ መንገድ ለመጠቀም አስፈላጊ ነው በማለት የሚገልፁት፡፡

የሰዋስውን አስፈላጊነት በተመለከተ ሁለት ዓይነት አመለካቶች አሉ፡፡ አንደኛው ሰዋስው ማለት የሕጎች ስብስብ ማለት ነው ይላል፡፡ ስለዚህ ቋንቋን በትክክል ለመጠቀም ልንማረው የሚገባ ነው ይላሉ፡፡ ሕጉን በትክክል ያልተማሩ ሰዎች የቋንቋውን ዝቅተኛ ቅርጽ ይጠቀማሉ፡፡ ይህ የትዕዛዛዊ ሰዋስው አመለካከት ነው፡፡ ሌላው አመለካት ደግሞ ሰዋስው ማለት ተናጋሪዎች የአፍ መፍቻ ቋንቋቸውን እንዲማሩና እንዲጠቀሙ የሚያስችላቸው ድብቅና ተፈጥሯዊ ችሎታ ነው፡፡ ለምሳሌ ህጻናት ለመናገር ሲሞክሩ ሕግን አይሸመድዱም ቋንቋቸው የሚገዛበትን ሥርዓት (Pattern) በተግባር ይማራሉ እንጅ፡፡ እናም ሰዋስው የቋንቋ ተጠቃሚዎች ኢ-ውሱን የሆኑ አዳዲስ ዓረፍተነገሮችን እንዲያፈልቁና እንዲረዱ የሚያስችል ነው፡፡ ይህም ገላጭ ሰዋስው (Descriptive Grammar) የምንለው ነው (ዲካፓ፣2008፣9)፡፡

ሰዋስዋዊ ስህተቶች በብዙ ሁኔታዎች የተግባቦትን ፍሰት ባይከለክሉም ትምህርታዊ ለሆኑ ጉዳዮች ግን የመግቢያ በር ጠባቂ (Gate Keepers) መሆናቸውን ማወቅ ይኖርብናል፡፡ ይኸውም በመጫወቻ ሜዳ ስህተት የሆነውን ተውላጠ ስም ወይም መስተዓምር መጠቀም ችግር የለውም፤ ነገር ግን ይህን ስህተት በአንድ የቃለ-መጠይቅ ቦታ መጠቀም ስህተት ነው (ኬክና ኪም፣ 2014፣23-24)፡፡

ከዚህ እንደምንረዳው ሰዋስው ተማሪዎችን ጥሩ የቋንቋ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያስችላቸዋል፡፡ ይኸውም ጥሩ ተናጋሪ፣ ጸሐፊ፣ እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል፡፡ ለዚህም ነው ብራውን (2000፣362) "ሰዋስው አያስፈልግም ብሎ የሚናገር፣ ተግባቦት እንዲሳካ ሰዋስው ቀዳሚ መሆኑን የሚጠራጠር አንድም የለም" በማለት የሚገልፁት፡፡

ኮርደር (1973) ደግሞ ከብራውን (2000፣362) ሃሳብ በተቃራኒ ተማሪዎች የተለያዩ የሰዋስው መዋቅሮችን አንፃራዊ በሆነ ሁኔታ ቋሚ እና ሁለንተናዊ (Universal) በሆነ ቅደም ተከተል ይለምዳሉ። ይኸውም ሰዋስውን ለመማር የሚያስችላቸውና የራሳቸው የሆነ አስቀድሞ የተዘጋጀ መርሐ-ትምህርት (Built-in-Syllabus) አላቸው በማለት ቢገልፁም ባይጌት (1994፣47) እና ካኒንግወርዝ (1984፣18) ግን የቋንቋ አጠቃቀም ሕግ (Rules of Use) ያለ ሰዋስዋዊ ሕግ (Rules of Grammar) ዋጋ የለውም በማለት ሃሳቡን ውድቅ ያደርጉታል። ለዚህም ነው ባዬ (2000፣xxv) የቋንቋን ሥርዓትና አጠቃቀም ያወቀ ተማሪ ከተራ ሹፌር እንደሚለይና እንዲያውም እንደ መካኒክ ሹፌር እንደሚቆጠር በመግለፅ ሥርዓቱንም ማወቅ የተሻለ የቋንቋ ተጠቃሚ እንደሚያደርግ የሚገልፁት። ይህም ለተለያዩ የክፍል ደረጃዎች ተብለው በተዘጋጁት የአማርኛ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የቀረቡትን የሰዋስው ይዘቶች ትክክለኛነት መፈተሽ አስፈላጊ መሆኑን ያመለክታል።

1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

ባይጌት (1994፣18) የሰዋስውን አስፈላጊነት በተመለከተ እንደሚያብራሩት መምህራን ሰዋስውን ማወቃቸው ተግባቦትንና ሥርዓትን ለየብቻ ለይተው ትኩረት እንዲሰጡ ያስችላቸዋል፤ ተማሪዎች የሚጥሟቸውን ሰዋስዋዊ ችግሮች መተንተን ይችላሉ፤ የተማሪዎችን የቋንቋ አጠቃቀም ከሰዋስው አንፃር በልበ ሙሉነት በተለይም ትክክለኛነቱን፣ ተገቢነቱን (Appropriateness) እና ገላጭነቱን (Expressiveness) መገምገምና ለተማሪዎች በተለያየ ደረጃ ግልፅ የሆነ የሰዋስው ትምህርት እንዴት ቀለል ተደርጎ መቅረብ እንዳለበት ለመረዳትና ለመተግበር ወዘተ እንደሚያስችል ይገልፃሉ።

ሰዋስውን ማስተማር አያስፈልግም የሚለው አመለካከት ከባድ የሆነ ፈተና እየገጠመው መሆኑን ይጠቁማሉ። በክፍል ውስጥ በሚሰጠው ተግባር ቅርፅ ላይ ማተኮር ዋጋ አለው የሚለው በስፋት ተቀባይነት እያገኘ ከመሆኑም በተጨማሪ ቋንቋውን ለተግባቦት ለመጠቀም ሰዋስው አስፈላጊ የሆነ ሀብት መሆኑን ይገልጻሉ (ኑናን፣1989፣ 13፤ ባይጌትና ሌሎች፣1994፣7)።

ጥንታዊ የሆነው መርሐ ትምህርት የተመሰረተው መዋቅራዊ ወይም ገላጭ ሰዋስው ላይ ነበር። መዋቅራዊ መርሐ ትምህርት ደግሞ ከፍች ይልቅ ለቅርፅ ትኩረት ይሰጣል። ለትምህርት የሚቀርበውን የሰዋስው ምርጫ በተመለከተ ግን በተማሪዎች በሚፈፀሙና በታወቁ ስህተቶች ላይ ማድረግ ጠቃሚ ነው። ምን እናስተምር የሚለው የሰዋስው ምርጫም ከተማሪዎች የእድገት ደረጃ አንፃር የሚወሰን ነው ይላሉ (ኤሊስ፣2006፣ 86-89)።

ሰዋስውን ለማስተማር ቅርፅ ተኮር ወይስ ፍች ተኮር ዘዴ ነው ተመራጭ የሚለውን በተመለከተ ግን አንፃራዊ በሆነ ሁኔታ ሁለቱም ዘዴዎች ውጤታማ መሆናቸውን የተለያዩ ጥናቶች እንዳመለከቱ ይገልፃሉ። ተማሪዎች በየትኛው ዘዴ ነው የበለጠ ተጠቃሚ የሚሆኑት ለሚለው ብዙ ተላውጦዎች ተፅዕኖ ያደርጋሉ። ለምሳሌ የቋንቋው መዋቅር ቀላል ከሆነ በቅርጽ ተኮር ዘዴ ማስተማር ተመራጭ ነው። የቋንቋው መዋቅር ውስብስብ ከሆነ ግን በፍች ተኮር ዘዴ ማስተማር የተሻለ ነው። በሰዋስዋዊ ትንታኔ ላይ ከፍተኛ ችሎታ ላላቸው ተማሪዎችም ቅርፅ ተኮር የሆነው ዘዴ ተመራጭ ነው (ኤሊስ፣2006፣98)።

በቅርፅ ተኮር ዘዴ ተማሪዎች ሕግን የሚማሩበትና ስለ ቋንቋው ገለፃ የሚደረግበት ነው። የቋንቋውን ሰዋሰዋዊ ሕግ የሚያስተምሩ የቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴዎች ለምሣሌ የሰዋሰው ወትርጉም ዘዴ ይህን የቅርፅ ተኮር መርህ ይከተላሉ (ኑናን፣1991፣156)። ዊዶዶ (2006፣122-141) የተባሉት ጸሐፊ "የሰዋስው ማስተማሪያ ሥልተ ትወራዎችና ዘዴዎች" በሚባለው ጽሑፋቸው እንዳቀረቡት ቅርፅ ተኮር ዘዴ ለብዙ ጊዜ በዓለም ላይ "የቋንቋ ማስተማር ዳቦና ቅቤ" (The Bread and Butter of language teaching) ተደርጎ እንደቆየ በመግለፅ አሁን ድረስ በብዙ የማስተማሪያ መጻሕፍት የበላይነቱን ይዞ የሚገኝ መሆኑን ይናገራሉ። ምክንያቱም ይህ አቀራረብ በቀጥታ ወደ ትምህርቱ ስለሚገባ ጊዜ ቆጣቢ ነው፤ ቅርፅን በተመለከተ በተብራራ ሁኔታ ለመግለፅና ወዲያውኑ ቀጥተኛ ምሣሌዎችን ለመስጠትም ያስችላል።

ግራንት (1987፣8-13) እንደሚሉት ፍፁም የሆነ የማስተማሪያ መጽሐፍ የለም። የማስተማሪያ መጽሐፍ እና የሥነ ዘዴ ምርጫ የሚወሰነው ተማሪዎች ቋንቋውን ለምንድን ነው የሚማሩት እና እንዴት ነው የሚማሩት በሚሉት ጉዳዮች ላይ ነው። እንዴት ነው የሚማሩት የሚለው ደግሞ የተማሪዎችን የተስተምህሮ ስልት (Learning Styles) የሚመለከት ጉዳይ መሆኑን በመጠቆም አንዳንዶች የጽሑፍ ዐውድ ያስደስታቸዋል፤ አንዳንድ ተማሪዎች ደግሞ የሰዋስው ሕጎች እንዲነገራቸው ከተቻለም በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው እንዲቀርብላቸው ይፈልጋሉ፤ ሌሎች ደግሞ የሰዋስው ሕግን አይፈልጉም። ስለዚህ መጽሐፉ የተማሪዎችን የመማር ስልት ያማከለ ቢሆን ይመረጣል።

የሰዋስው ይዘቶችን ትክክለኛነት በተመለከተ ጌታሁን (2025) ካደረገው ጥናት ውጭ የተሰሩ ስራዎችን ማግኘት አልተቻለም። ይህም ለዚህ ጥናት ዋናው አነሳሽ ምክንያት ሆኗል። ጌታሁን (2025) ያደረጉት ጥናት ዋና ዓላማ በ2014 ዓ/ም ታትመው በ2015 ዓ/ም ሥራ ላይ በዋሉት ከ7ኛ እስከ 10ኛ ክፍል ባሉት የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የቀረቡትን የሥነልሳን ይዘቶች

ሰዋስዋዊነት መገምገም ነበር። በዚህ ጥናት አማርኛን እንደአፍ መፍቻና እንደሁለተኛ ቋንቋ ለማስተማር በክልሎችና በከተማ አስተዳድር ትምህርት ቢሮዎች እንደዚሁም በትምህርት ሚኒስቴር በተዘጋጁት የአማርኛ መማሪያ መጻሕፍትና በመምህሩ መምሪያ ውስጥ የቀረቡትን የሥነልሳን ይዘቶች ሰዋስዋዊነት ለመገምገም የሚያስችሉ መረጃዎች በሰነድ ፍተሻ ተሰብስበዋል።

የተሰበሰቡት መረጃዎች ምዕላድ፣ሀረግና ዓረፍተ ነገር በሚሉ ቅደም ተከተሎች ተደራጅተው በገላጭ የምርምር ዘዴ ከተተነተኑ በኋላ የተገኙት ውጤቶች፣ አብዛኛዎቹ የሥነልሳን ይዘቶች የቋንቋን ሥርዓት ጠብቀው የቀረቡ ሲሆን የተወሰኑት ግን የቋንቋውን ሰዋስዋዊ ባህሪ ያጡ ሆነው ተገኝተዋል። ከዚህ ውጤት በመነሳት መማሪያ መጻሕፍቱ ለወደፊት በሚዘጋጁበት ጊዜ የተለያዩ ሙያተኞችን (ለምሳሌ የስነዘዴ፣ የሥነልሳን) ባካተተ መልኩ መሆን እንዳለበትና የደቦና የኮሚሽን ሥራ ሳይሆን ሙያዊ ግዴታና ሀላፊነትን ባስቀደመ መንገድ መዘጋጀት እንዳለባቸው ገልፀዋል።

ሌላው መጻሕፍቱ ታትመው ከመሰራጨታቸው በፊት ለሥራው ቅርበት ባላቸው ሙያተኞች እንዲገመገሙ ቢደረግ የሚሉ አስተያየቶችን በመስጠት ጥናታቸውን አጠናቀዋል። ከዚህ በመነሳት ለመሆኑ በአንደኛ ደረጃ በተለይም ለ5ኛ እና ለ6ኛ ክፍሎች የተዘጋጁ የአማርኛ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የቀረቡት የሰዋስው ይዘቶችስ ትክክለኛነት ምን ይመስላል የሚለውን መገምገም አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል።

2. የጥናቱ ዘዴ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ ለ5ኛ እና ለ6ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋን እንደ አፍ መፍቻና እንደሁለተኛ ቋንቋ ለማስተማር በተዘጋጁት መጻሕፍት ውስጥ የቀረቡትን የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች (ሥነምዕላድ/ቃል፣ ሀረግና ዓረፍተ ነገር) ከትክክለኛነት አንፃር መገምገም ነው። ይህን ዓላማ ለማሳካት በአማራ ፣በኦሮምያ፣በደቡብ ክልሎች እና በአዲስ አበባ አስተዳደር ትምህርት ቢሮዎች ለ5ኛ እና ለ6ኛ ክፍል የተዘጋጁት የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት በዓላማ ተኮር የንሞና ዘዴ የመረጃ ምንጭ በመሆን ተመርጠዋል። በእነዚህ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የቀረቡት የሰዋስው ይዘቶች በሰነድ ፍተሻ ተሰብስበዋል። የተሰበሰቡት መረጃዎች ስነምዕላድ፣ቃል፣ሀረግና ዓረፍተ ነገር በሚሉ ቅደም ተከተሎች ከተደራጁ በኋላ ዓይነታዊ በሆነ መንገድ ተተንትነው ቀርበዋል።

3. የመረጃ ትንተና

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በ5ኛ እና 6ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋን እንደ አፍ መፍቻና እንደሁለተኛ ቋንቋ ለማስተማር በተዘጋጁት መጻሕፍት ውስጥ የቀረቡትን የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች (ሥነምዕላድ/ቃል፣ ሀረግና ዓረፍተ ነገር) ከትክክለኛነት አንፃር መገምገም ነው። በመሆኑም በተለያዩ ክልሎች እና የከተማ አስተዳድር ትምህርት ቢሮዎች የተዘጋጁትን መማሪያ መጻሕፍት ከሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ትክክለኛነት አንፃር ከሥነምዕላድ/ቃል፣ ሀረግና ዓረፍተ ነገር አንፃር በቅደም ተከተል እንደሚከተለው ይቀርባሉ።

3.1. ስነምዕላድ

ምዕላድ ሲባል ትርጉም ያለውና ወደ አነስተኛ ቅንጣት ሊከፈል የማይችል አሀድ ማለት ነው (ጌታሁን፣1990)። ይህን በተመለከተ በተለያዩ ክልሎች እና የከተማ አስተዳድሮች ለአምስተኛ እና ለስድስተኛ ክፍል የተዘጋጁትን የምዕላድ ጥያቄዎችና ማብራሪያዎች እንመልከት።

"ጥገኛ ምዕላዱን ከዋና ቃሉ ለይታችሁ አስቀምጡ።" ምሳሌ:- መንገደኛ = መንገድ - ኛ   አስደነገጠ = አስ-ደነገጠ (አ/አ መስተዳድር 6ኛ፣11)። "ደነገጠ" የሚለው ቃል ግን ነፃ ምዕላድ አይደለም። ምክንያቱም -ኧ የሚል ቅጥያ ምዕላድ አለውና።

"ቀጥሎ ተነጣጥለው የቀረቡትን ምዕላዶች በማጣመር ቃላት መስርቱ።"

ረ. በ-ጥልቅ-ኧ-ት

ሰ. በ-አደገ-ች-በት (አ/አ መስተዳድር 6 ኛ፣ 21)።

ከላይ ከቀረበው ጥያቄ እንደምንመለከተው በ "ሰ" ላይ የቀረበው የምዕላድ አከፋፈል ትክክል አይደለም፤ ምክንያቱም የምዕላዱ አከፋፈል በ-አደግ-ኧች-ብ-ኧት ተብሎ ነበር መከፈል ያለበት።

“ የሚከተሉትን ቃላትና ሐረጋት ምሳሌውን መሰረት በማድረግ በዋና ቃል ላይ ድህረ ግንድ ቅጥያዎችን እያጣመራችሁ ጻፉ፡፡“

ሐ. መከረ-ኣት

መ. ተከሰተ-ኧች (አ/አ መስተዳድር6ኛ፣73)፡፡

ከላይ ከቀረበው ጥያቄ እንደምንመለከተው በ “ሐ” እና “መ“ ላይ የቀረበው የምዕላድ አከፋፈል ትክክል አይደለም፤ ምክንያቱም በ “ሐ” የቀረበው የምዕላድ አከፋፈል **መከር-ኧ-ኣት** እና በ “መ“ የቀረበው ደግሞ **ተ-ከሰት-ኧች** ተብሎ ነበር መከፈል ያለበት፡፡

“ የሚከተሉትን ምእላዶች አጣምራችሁ በመፃፍ አንብቡ፡፡“

ሠ. እ-ሰራ-በት-አለሁ (አ/አ መስተዳድር6ኛ፣114)፡፡

የአማርኛ ግሶች ባህሪ የመዋቅር ውስብስብነት እንዳላቸው እየታወቀ ስለ ነፃ ምዕላድ እና ቅጥያ ምዕላድ ለማስተማር ግሶችን ሳይሆን ሌሎችን የቃል ክፍሎች ቅድሚያ መስጠት ያስፈልግ ነበር፡፡ ለዚህ ማሳያ የሚሆነው ከላይ በ “ሠ“ ላይ የቀረበውን ቃል አከፋፈል ስንመለከት ትክክል አይደለም፡፡ ምክንያቱም የግስ አምዱ ላይ የባለቤት አመልካች አፀፋ (-ኣ)፣ ረዳት ግሱ -አል ላይ ደግሞ መደብ አመልካች ምዕላድ (-ኧሁ) አንድ ላይ እንደ አንድ ምዕላድ ሆነው ቀርበዋል፡፡ እናም ከላይ የቀረበው የምዕላድ አከፋፈል **እ-ሰር-ኣ-ብ-ኧት-አል-ኧሁ** ተብሎ ነበር መቅረብ ያለበት፡፡

ሰንጠረዡ 1. “…ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት ቃላት ውስጥ ዋናውን ቃልና ቅጥያውን ለይታችሁ በማውጣት አሳዩ፡፡“

ቃል	ዋና ቃል	ቅጥያ
መጣችሁ	መጣ	-ኣችሁ

(ደቡብ ክልል 6ኛ፣59)፡፡

“ በሚከተሉት ውስብስብ ቃላት/ሀረጋት ውስጥ ያሉ ምዕላዶችን ለይታችሁ አንብቡ፡፡“

ምሳሌ፡- እየሮጠች= እየ-ሮጠ-ች

አልጠጣም= አል-ጠጣ-ም (ኦሮምያ ክልል 6ኛ፣ 19)፡፡

“ከዚህ በታች በምዕላድ ተነጣጥለው የተፃፉትን ቃላት በደብተራችሁ ላይ እያጣመራችሁ በመፃፍ አንብቡ፡፡“

ምሳሌ፡- እየ- አጨበጨብ-ኣችሁ-ልን (አ/አ መስተዳድር 5ኛ፣125)፡፡ ይህን ጥያቄ የደቡብ ክልል ለ5ኛ ክፍል ባዘጋጀው መማሪያ መፅሐፍ ገፅ 132 ላይ ተደግሞ እናገኘዋለን፡፡

ከላይ ከቀረበው ጥያቄ እንደምንመለከተው የደቡብ ክልል “መጣ” የሚለውን ቃል ዋና ቃል በማለት ነፃ ምዕላድ በማድረግ ሲያቀርበው የኦሮሚያ ክልል ባዘጋጀው መፅሐፍ ደግሞ “ሮጠ”፣”ጠጣ” የሚሉ ቃላትን አንድ ምዕላድ በማድረግ አቅርቦታል፡፡ የአዲስ አበባ መስተዳደር ባዘጋጀው የ5ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ “እየአጨበጨባችሁልን” የሚለውን ቃል በምዕላድ የከፋፈለበት መንገድ ትክክል አይደለም፡፡ ይኸውም “**እየ-አጨበጨብ-ኣችሁ-ል-ን”** ተብሎ ነበር መከፈል ያለበት፡፡ ይህም -ል በእኔ ፍልጎት የሚለውን ትርጉም የያዘ ሲሆን “እንደ-አይ-ጨናገፍ-ብኝ” በሚል ደቡብ ክልል 5ኛ ክፍል ገጽ 132 ላይ የቀረበው ደግሞ እንደ-አል-ይ-ጨናገፍ-ብ-ኝ በሚል መቅረብ ነበረበት፡፡ በዚህም አከፋፈል -ብ ያለ እኔ ፍላጎት የሚል ትርጉም አለው፡፡

“ከዚህ በታች ያለውን ሰንጠረዥ በደብተራችሁ ላይ በማዘጋጀት ተነጣጥለው የተፃፉትን ቃላት እያጣመራችሁ በመፃፍ አንብቡ፡፡“

ሀ. ስለ-ሄደ-ች

ለ. የ- ተ-መለሰ-ው (አ/አ መስተዳድር 5ኛ፣143)፡፡

በ “ሀ” የቀረበው የምዕላድ አከፋፈል ስለ-ሄድ-ኧች በ “ለ” ላይ የቀረበው የምእላድ አከፋፈል ደግሞ የ-ተ-መለስ-ኧ-ው ተብሎ ነበር መቅረብ ያለበት።

“ ከዚህ በታች ተነጣጥለው የተፃፍትን ቃላት እያጣመራችሁ በመፃፍ አንብቡ።“

ሀ. ስለ- ሄደ-ች (ደቡብ ክልል 5ኛ፣152)።

“የሚከተሉትን ቃላትና ሐረጋት በመነጣጠልና በማጣመር አንብቡ።“

መ. እንደ-አስ-ጀመሩ-ት

ሠ. እየ-ተደረገ-ልኝ (አማራ ክልል 5ኛ፣14)።

“ …የሚከተሉትን ቃላትና ሐረጋት በመነጣጠልና በማጣመር አንብቡ።“

ሀ. በ-ዝናብ-ኣማ-ነቱ

ለ. እየ-ተ-ጠቀመ-በት (አማራ ክልል 5ኛ፣34)።

ከላይ ለማቅረብ እንደተሞከረው እንደቅደም ተከተላቸው የደቡብ ክልል በ”ሀ”፣ የአማራ ክልል በ “መ” “ሠ”፣ “ሀ”፣ እና “ለ” ላይ የቀረቡት ቃላት/ሀረጋት በምዕላድ የተከፋፈሉበት መንገድ ትክክል አይደለም። ይኸውም “ስለሄደች” የሚለው “ስለ-ሀየድ-ኧች”፣ “ጀመሩ” የሚለው “ጀመር-ኡ”፣ “በዝናባማነቱ” የሚለው “በ-ዝናብ-አማ-ነት-ኡ”፣ “እየተጠቀመበት” የሚለው ቃል ደግሞ “እየ-ተ-ጠቀም-ኧ-ብ-ኧት” ተብሎ መከፋፈል ነበረበት። ስለምዕላድ አከፋፈል የቀረቡት ጥያቄዎች አብዛኛዎቹ ግስ ላይ ያተኮሩ ናቸው። የአማርኛ ግሶች ደግሞ ምእላዳዊ ውስብስብነት የሚታይባቸው ናቸው። እናም ግስ ላይ ያተኮሩ የምዕላድ ጥያቄዎችን በኮሌጅና በዩኒቨርሲቲ ደረጃ ማቅረብ የተሻለ አማራጭ ይሆን ነበር። ይህን ለማሳየት የአማራ ክልል ለ5ኛ ክፍል ባዘጋጀው መማሪያ መጽሐፍ ገጽ 41 ላይ “በማጣመር አንብቡ“ በሚል የቀረቡትን ተጨማሪ ጥያቄዎች መመልከት ይቻላል።

ሀ. ኣል-አረረ-ብኝ-ም ሐ. ስለ-ተካንኩ-በት

ለ. ከ-አ-ቀረበ-ች-ው መ. የ-ተ-ወቀጠ-ው-ን

ከላይ ከቀረቡት ጥያቄዎች እንደምንመለከተው “አላረረብኝም” የሚለው ቃል “አል-አረር-ኧ-ብ-ኝ-ም”፣ “ከአቀረበችው” የሚለው “ከ-አ-ቀረብ-ኧች-ው”፣ “ስለተካንኩበት” የሚለው “ስለ-ተካን-ኩ-ብ-ኧት”፣ “የተወቀጠውን” የሚለው ጥገኛ ሀረግ ደግሞ “የ-ተ-ወቀጥ-ኧ-ው-ን” በሚል ተከፋፍለው መቅረብ ነበረባቸው።

3.2. የቃል ክፍል

ከዚህ በመቀጠል ደግሞ የቃል ክፍልን በተመለከተ የቀረቡ ምሳሌዎችንና ጥያቄዎችን ለማት እንሞክራለን።

“ በሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ተውሳከ ግስ የሆኑትን ቃላት ለይታችሁ ፃፉ።“

ምሳሌ፡- ሀ. ካሳ ነገ ይመጣል።

ሐ. ሰብለ በፍጥነት ተመለሰች።

ሠ. መጽሐፉ እዚህ አለ። (አ/አ መስተዳድር 5ኛ፣40)።

ከላይ ከቀረቡት ጥያቄዎች ለማየት እንደሚቻለው በ“ሀ” ላይ በቀረበው ዓ/ነገር ውስጥ የግስ ገላጭ በመሆን ያገለገለው “ነገ” የሚለው ሲሆን የቃል ክፍሉ ግን ተውሳከ ግስ ሳይሆን ስም ነው። በ”ለ” ላይ በቀረበው ዓ/ነገር ውስጥም ከሁኔታ አንፃር የግስ ገላጭ በመሆን ያገለገለው “በፍጥነት” የሚለው መስተዋድዳዊ ሀረግ (በ- የሚለው መስተዋድድና ፍጥነት የሚለው ስም) እንጅ የቃል ክፍሉ ተውሳከ ግስ አይደለም። በ”ሠ” ላይ በቀረበው ዓ/ነገር ደግሞ “እዚህ” የሚለው ከቦታ አንፃር ጠቋሚ መስተዓምር እንጅ ተውሳከ ግስ አይደለም።

" የሚከተሉትን ተውሳከ ግሶች በመጠቀም ዓረፍተ ነገር መስርቱ።"

ምሳሌ:- ዳንኤል ጠዋት ተመለሰ።

ሀ. ትናንት ለ. ዘንድሮ ሐ. ቅድም መ. ቶሎ ሠ. ማታ ረ. ጥንት

(አ/አ መስተዳድር 5ኛ፣41)።

ከላይ ከቀረበው ምሳሌ ለማየት እንደሚቻለው ጠዋት የሚለው ስም የግስ ገላጭ በመሆን ሲያገለግል የቃል ክፍሉ ግን ተውሳከ ግስ አይደለም። ከ"ሀ" እስከ "ረ" የቀረቡትን ጥያቄዎች ስንመረምርም ከ "ቶሎ" በስተቀር ሌሎች ቃላት የቃል ክፍላቸው "ስም" ነው።

" በሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ የሚገኙትን የሁኔታ ተውሳከ ግሶች አውጥታችሁ ምክንያቱን አብራሩ። "

ምሳሌ:- አየለ በፍጥነት ተመለሰ።

ለ. መሀመድ በድንገት መጣ። መ. ረሂማ በቁጣ ተናገረች።

ሐ. ሄኖክ እየሮጠ ሄደ። ሠ. ልዑል አምርሮ አለቀሰ። (አ/አ መስተዳድር 5ኛ፣51)።

የአዲስ አበባ መስተዳድር ለ5ኛ ክፍል ባዘጋጀው የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ለማየት እንደሚቻለው የሁኔታ ተውሳከ ግስ ተብለው የቀረቡት ምሳሌዎችና ጥያቄዎች ሁሉም ስህተት ያለባቸው ናቸው። ይኸውም ከምሳሌው ብንጀምር "በፍጥነት" የሚለው መስተዋድዳዊ ሀረግ ነው። በ"ለ" እና በ"መ" ላይ የቀረቡት "በድንገት" (በ-የሚለው መስተዋድድ እና ድንገት የሚለው ስም) እና "በቁጣ" (በ-የሚለው መስተዋድድ እና ቁጣ የሚለው ስም) መስተዋድዳዊ ሀረግ ናቸው። በ"ሐ" እና በ"ሠ" ላይ የቀረቡት "እየሮጠ" እና "አምርሮ" የሚሉት ደግሞ ጥገኛ ዓረፍተ ነገሮች እንጅ ተውሳከ ግሶች አይደሉም።

በኦሮምያ ክልል 5ኛ ክፍል ገፅ 41፣ በተዘጋጀው የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ስለ ተውሳከ ግስ የሚከተለው ምሳሌ ቀርቧል።

-ፍራኦል ትናንት መጣ።

-ቦንቱ እዚህ ነበረች።

- ዘይነባ በፍጥነት መጣች።

የመጀመሪያውን ምሳሌ ስናይ "ትናንት" የሚለው የግስ ገላጭ ሲሆን የቃል ክፍሉ ግን "ስም" ነው። "ትናንት" በሚለው ምትክ "ቅዳሜ" የሚለውን ቃል በመተካት ዓረፍተ ነገሩን "ፍራኦል ቅዳሜ መጣ::" ማለት ይቻላልና። በሁለተኛው ምሳሌ ላይ የቀረበው "እዚህ" የሚለው ቃልም ከቦታ አንፃር ጠቋሚ መስተዓምር ነው። በሶስተኛው ምሳሌ ላይ የቀረበው "በፍጥነት" የሚለውም መስተዋድዳዊ ሀረግ እንጅ ተውሳከ ግሶች አይደሉም።

" የሁኔታ ተውሳከ ግስ ማለት በግሱ የተገለጸው ድርጊት እንዴት እንደተፈፀመ የሚያመለክት ነው።

ምሳሌ:- ፋጡማ በዝግታ ተራመደች። (ኦሮምያ ክልል 5ኛ፣55)።

የደቡብ ክልል ያዘጋጀው የ5ኛ ክፍል መጽሀፍ ውስጥ ገፅ 52 ላይ ስለ ሁኔታ ተውሳከ ግስ የሚከተለው ምሳሌ ቀርቧል። አየለ ከሄደበት በፍትነት ተመለሰ።

" የሚከተሉትን ሁኔታ አመልካች ተውሳከ ግሶች በመጠቀም ዓረፍተ ነገሮችን መስርቱ። "

1. በፍጥነት 2. በድንገት 3. በጀግንነት 4. በትጋት 5. ምንኛ 6. እየሮጠች 7. በቀስታ (ኦሮምያ ክልል 5ኛ፣55)።

ከላይ ለማሳየት እንደተሞከረውና የኦሮምያ እና የደቡብ ክልል ትምህርት ቢሮዎች ለ5ኛ ክፍል ባዘጋጁቸው መጻሕፍት ውስጥ እንደቅደም ተከተላቸው "በዝግታ" እና "በፍጥነት" የሚሉትን መስተዋድዳዊ ሀረጎች የሁኔታ አመልካች ተውሳከ ግስ በሚል

ተጠቅሰዋል። በመቀጠልም በኦሮምያ ክልል የተዘጋጁትንና ከ1ኛ እስከ 7ኛ ተራ ቁጥር ድረስ የቀረቡትን ጥያቄዎች ስናይ “ምንኛ” ከሚለው ውልድ ስምና “እየሮጠ” ከሚለው ጥገኛ ዓረፍተ ነገር በስተቀር ሁሉም መስተዋድዳዊ ሀረጎች ናቸው።

“ …በሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ተውሳከ ግሶችን ለይታችሁ ጻፉ።“

ሀ. አያቴ ስለሞተች እጅግ አዘንኩ።
ለ. ነጎድጓዱ ድንገት ሲያንባርቅ ክፉኛ ደነገጠ።
ሐ ሳንካ ስለገጠመው ትዳሩ እያሰበ ብዙ ጠጣ።
መ. ፋቱማ ቶሎ መጣች።
ሠ. ተመስገን ከአሜሪካ ትናንት መጣ። (አማራ ክልል 6ኛ፣56)።

ከላይ ለማሳየት እንደተሞከረው የአማራ ክልል ትምህርት ቢሮ ለ6ኛ ክፍል ባዘጋጀው የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ በ”ሀ” ላይ የቀረበው “ስለሞተች” የሚለው ጥገኛ ዓ/ነገር ሲሆን ከምክንያት አንፃር የግስ ገላጭ ነው። “እጅግ” የሚለው ደግሞ ድግሪ አመልካች መስተዓምር ነው። በ“ለ” ላይ በቀረበው ዓ/ገር “ነጎድጓዱ ድንገት ሲያንባርቅ” የሚለው ጥገኛ ዓ/ነገር ከጊዜ አንፃር፣ “ክፉኛ” የሚለው ውልድ ተውሳከ ግስ ደግሞ ከሁኔታ አንፃር የግስ ገላጭ ናቸው። በ “ሐ” ላይ በቀረበው ዓ/ነገር ደግሞ “ትዳሩ ሳንካ ስለገጠመው እያሰበ” የሚለው ጥገኛ ዓ/ነገር ከምክንያት አንፃር የግስ ገላጭ ነው። “ብዙ” የሚለው ደግሞ ከመጠን አንፃር መስተዓምር ነው። በ”መ” ላይ የቀረበው “ቶሎ” የሚለው ቃል ግን እንደ “ክፉኛ” ሁሉ ከማንነትም ሆነ ከአገልግሎት አንፃር ትክክለኛ ተውሳከ ግስ ነው። በመጨረሻም በ”ሠ” ላይ የቀረበው “ከአሜሪካ” የሚለው መስተዋድዳዊ ሀረግ ከቦታ አንፃር “አጎላማሽ” ወይም የግስ ገላጭ ሲሆን “ትናንት” የሚለው ስም ደግሞ ከጊዜ አንፃር የግስ ገላጭ ናቸው እንጅ ተውሳከ ግሶች አይደሉም።

“በሚከተሉት ተውሳከ ግሶች የተሟሉ ዓረፍተ ነገሮችን መስርቱ።“

እዚያ፣ ትንሽ፣ ክፉኛ፣ ቶሎ፣ እዚህ፣ አምና (አማራ ክልል 6ኛ፣68)።

ከዚህ ላይ እንደሚታየው ግን “ክፉኛ” እና “ቶሎ” ከሚሉት ቃላት በስተቀር ሌሎች ቃላት ተውሳከ ግሶች አይደሉም። ይኸውም “እዚያ”፣ “እዚህ” የሚሉት ጠቋሚ መስተዓምሮች ሲሆኑ “ትንሽ” የሚለው ቃል ቅፅል ነው። “አምና” ቃል የሚለው ደግሞ ስም ነው።

ሰንጠረዥ 2. ሰንጠረዡን በደብተራችሁ አዘጋጅታችሁ የተውሳከ ግስ ዓይነቶቹን በምሳሌው መሰረት አመልክቱ።

ተውሳከ ግስ	የጊዜ	የቦታ	የመጠን	ሁኔታ
ቶሎ	x			
በጣም				
ክፉኛ				
ወደዚያው				
ወዲያው				
ሌሊት				

(አማራ ክልል 6ኛ፣81)።

ከላይ ከቀረበው ሰንጠረዥ እንደምንመለከተው “ቶሎ” እና “ክፉኛ” ከሚሉት ቃላት ውጭ የቀረቡት ተውሳከ ግሶች አይደሉም።

“ በሚከተሉት ዓ/ነገሮች ቅጽሎችን ለይታችሁ በማውጣት ጻፉ።“

ሠ. የካቲት 23፣ ለኢትዮጵያ ታሪካዊ ቀን ነው። (አማራ ክልል 6ኛ፣138)።

በአማርኛ ቋንቋ “ቅጽል” በሚል የሚታወቁት ቃላት ከተውሳከ ግስ አንፃር ሲታዩ የተሻለ ቁጥር ያላቸው ቢሆንም የአማራ ክልል ትምህርት ቢሮ ለ6ኛ ክፍል ባዘጋጀው የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ እንደቀረበው ግን እጅግ አነስተኛ ትኩረት ነው የተሰጣቸው።ለአብነት የቀረቡትም ቢሆን በትክክለኛው መንገድ አይደለም። ለዚህ ማሳያ የሚሆነው ከላይ በ”ሠ” ላይ የቀረበውን ዓ/ነገር ስናይ “ታሪካዊ” የሚለው ቃል የስም ገላጭ እንጅ “ቅጽል” አይደለም።

" በሚከተሉት ዓ/ነገሮች ውስጥ ያሉትን የጊዜ ተውሳከ ግሶች ለይታችሁ ፃፉ፡፡"

ምሳሌ፡- ዛሬ፣ በኋላ፣ አሁን፣ ነገ

- አለሚቱ ባለፈው ዓመት ከ5ኛ ክፍል አንደኛ ወጣች፡፡
- ሀሚድ ትምህርት ቤት በጧት ያደርሳል፡፡
- ወይዘሮ በለጡ ትናንት ህጻናትን ስለመልካም ሥነምግባር አስተማሩ፡፡
- መገርሳ ዛሬ ጧት በቀጠሮው መሰረት ከቦታው ደረሰ፡፡
- መቅደስና ሪሃና በሚቀጥለው ዓመት ወደ ሀዋሳ ለመሄድ ተስማሙ፡፡
- ነብዩ ባለፈው ሳምንት ቤተሰቦቹን ጠይቆ ተመለሰ፡፡
- ወታደር ዘወትር የሀገሩን ሰላም ለማስከበር ዘብ የቆመ ነው፡፡
(አ/አ መስተዳድር 6ኛ፣40)፡፡

ስለ ተውሳከ ግስ የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር ለ6ኛ ክፍል ያዘጋጀው የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍም ተመሳሳይ ችግሮች ያሉበት ነው፡፡ ለዚህ ማሳያ የሚሆኑ ከላይ የቀረቡትን ምሳሌዎችንና ጥያቄዎችን እንመልከት፡፡ ከላይ በምሳሌነት የቀረቡትን ዓ/ነገሮች ስናይ "ባለፈው ዓመት"፣ "በጧት"፣ "በሚቀጥለው ዓመት"፣ "ባለፈው ሳምንት" የሚሉት መስተዋድዳዊ ሀረጎች ከጊዜ አንፃር የግስ ገላጭ ሲሆኑ "ትናንት"፣ "ዛሬ"፣ "ጧት"፣ "ዘወትር" የሚሉት ስሞች ደግሞ አሁንም ከጊዜ አንፃር የግስ ገላጮች እንጅ ተውሳከ ግሶች አይደሉም፡፡ ሌሎች ተጨማሪ ጥያቄዎችን እንመልከት፡፡

" ቀጥለው ከቀረቡታ ቃላትና ሐረጋት የጊዜ ተውሳከ ግስ የሆኑትን ለይታችሁ ፃፉ፡፡"

-ወዲያውኑ - አሳዛኝ -ዛሬ -በመኪና አደጋ -ስለረበሹ -ነገ -አሁን -ጥሩ -አስደሳች -ሌሊት - ትምህርት ቤት -ያለፈው ዓመት (አ/አ መስተዳድር 6ኛ፣41)፡፡

" የሚከተሉትን የጊዜ ተውሳከ ግሶች በመጠቀም ዓ/ነገር ሰርታችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡"

ሀ. አምና ሠ. ሌሊት

ለ. ባለፈው ሳምንት ረ. ቶሎ ቶሎ

ሐ. ከወር በኋላ ሰ. አልፎ አልፎ

መ. የዛሬ ዓመት ሸ. በዚህ ዓመት (አ/አ መስተዳድር 6ኛ፣56)፡፡

ከላይ ከቀረቡት ጥያቄዎች ለማየት እንደሚቻለው የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር ለ6ኛ ክፍል ባዘጋጀውና ገጽ 41 እና 56 ላይ ከቀረቡት ቃላትና ሀረጋት ውስጥ ከ"ቶሎ ቶሎ" ውጭ የግስ ገላጮች እንጅ አንዳቸውም ተውሳከ ግስ አይደሉም፡፡ ይኸውም የቃል ክፍላቸው ስም (ለምሳሌ ሌሊት፣አምና፣ነገ)፣ ቅፅል (ለምሳሌ ጥሩ፣አስደሳች፣አሳዛኝ ወዘተ.)፣ ስማዊ ሀረግ (ለምሳሌ ትምህርት ቤት፣ ያለፈው ዓመት፣ የዛሬ ዓመት ወዘተ.)፣ መስተዋድዳዊ ሀረግ (ለምሳሌ በመኪና አደጋ፣ ከወር በኋላ፣ በዚህ ዓመት ወዘተ.) እና ጥገኛ ሀረጎችን (ለምሳሌ ስለረበሹ) አጠቃሎ የያዘ ነው፡፡

"ከዚህ በታች የቀረቡትን ቃላት የትኛውን ጾታ እንደሚያመለክቱ በቡድን በመሆን ለዩ፡፡"

ምሳሌ፡- **ቃል** **ጾታ**

ልጅ ወንድ/ተባዕታይ (ደቡብ ክልል 6ኛ፣56)፡፡

"በሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ የተሰመረባቸው ቃላት ከየትኛው የቃል ክፍል እንደሚመደቡ ለይታችሁ ፃፉ፡፡"

ሐ. ዳንችሌ <u>ትምህርት ቤት</u> ሄደች (ደቡብ ክልል 6ኛ፣117)፡፡

ከዚህ እንደሚታየው የደቡብ ክልል ለ6ኛ ክፍል ባዘጋጀው የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ በ"ሐ" ላይ እንደሚታየው የተሰመረበት ስማዊ ሀረግ ሆኖ ሳለ የቃል ክፍሉን እንዲናገሩ መጠየቃቸው ትክክል አይደለም። "ልጅ" የሚለውን ቃል ለምን የተባዕታይነት ፆታ ያመለክታል እንደተባለም ግልፅ አይደለም። "ሴት ልጅ ወለደ" ማለት ይቻላልና።

3.3. ስነሀረግ

በዚህ ንዑስ ክፍል ደግሞ ሀረግን በሚመለከት የቀረቡትን ምሳሌዎችና ጥያቄዎች አንድ በአንድ ለማየት እንሞክራለን።

" ቀጥሎ የቀረቡትን ሐረጎች ስማዊና ግሳዊ በማለት ከፋፍሏቸው።"

ታላላቆቻችንን በአግባቡ መታዘዝ (ኦሮምያ ክልል 5ኛ፣34)።

"መስተዋድዳዊ ሀረግ ማለት ከመሪው መስተዋድድና ከሌሎች ተዋቃሪ አካላት ጋር የሚመሰረት የሀረግ ዓይነት ነው።"

ምሳሌ፡- ስለ ገባ (ኦሮምያ ክልል 5ኛ፣103)።

ኦሮምያ ክልል ትምህርት ቢሮ ባዘጋጀው የ5ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ገጽ 34 እና 103 ላይ ከቀረበው ጥያቄና ምሳሌ ላይ ማየት እንደሚቻለው "ታላላቆቻችንን በአግባቡ መታዘዝ" የሚለው ጥያቄ ስማዊ ሀረግ ብቻ ነው። ምክንያቱም መሪው መታዘዝ የሚለው አርዕስት (ስም) ነውና። ሌላው ስለ መስተዋድዳዊ ሀረግ ምሳሌ ተደርጎ ቀረበው "ስለገባ" የሚለው የጥገኛ ዓ/ነገር እንጅ የመስተዋድዳዊ ሀረግ ምሳሌ ሊሆን አይችልም። ምክንያቱም መስተዋድዳዊ ሀረግ ከመሪው መስተዋድድና መሙያ ከሆነ ስም ወይም ከመስተዋድዳዊ ሀረግ ጋር የሚዋቀር ሀረግ ነውና። በመሆኑም "ስለገባ" የሚለው የጥገኛ ዓ/ነገር ምሳሌ እንጅ የመስተዋድዳዊ ሀረግ ምሳሌ ሊሆን አይችልም።

3.4. ዓረፍተ ነገር

ከዚህ በመቀጠል ደግሞ ስለ ዓረፍተ ነገር የቀረቡትን ማብራሪያዎች፣ ምሳሌዎችና ጥያቄዎች ከየክፍል ደረጃው በማቅረብ ለማየት እንሞክራለን።

"…ስም በዓ/ነገር ባለቤትነት የሚያገለግለው የቃል ክፍል ሲሆን በማሰሪያ አንቀፅነት የሚያገለግለው የቃል ክፍል ደግሞ ግስ ነው። ዓ/ነገር ማለትም ሙሉ ሃሳብ የሚያስተላልፍ አነስተኛ የድርሰት ክፍል ነው" ይላል። ከቀረቡት ጥያቄዎች ውስጥ "ማር እወዳለሁ" የሚለው አንዱ ነው (አ/አ መስተዳድር 5ኛ፣82)።

"ማር እወዳለሁ" በሚለው ዓረፍተ ነገር ውስጥ "ማር" ስም ሲሆን ባለቤት ግን አይደለም። ሌላው ዓ/ነገር ለሚለው ብያኔ የተሰጠው ገለፃም ትክክል አይደለም። ምክንያቱም ዓ/ነገር ለመባል የግድ ሙሉ ሃሳብ የሚያስተላልፍ መሆን የለበትም። ለምሳሌ ቁርሱን ሲበላ… የሚለው ዓ/ነገር ነው፤ ነገር ግን ሙሉ ሃሳብ አያስተላልፍም። ይህን ብያኔ ብቻ የምንቀበል ከሆነ ጥገኛ ዓ/ነገር የሚባል መኖር የለበትም ነበር።

" የአሁን ጊዜ ግስ የሚባለው አንድ በአሁኑ ጊዜ የሚፈፀም ወይም በመፈፀም ላይ ያለ ድርጊትን ወይም ሁኔታን የሚያመለክት የጊዜ ዓይነት ነው ካለ በኋላ የአሁን ጊዜ ግስ "እየ-"የሚል ምዕላድ ሊያስቀድምና "ነው" የሚል ረዳት ግስ ሊያስከትል ይችላል" ይላል።

ምሳሌ፡- ተማሪዋ ወደ ትምህርት ቤት እየሄደች ነው።

-ልጁ ልብሱን እያጠበ ነው (አ/አ መስተዳድር 5ኛ፣130)።

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት ምሳሌዎች የደቡብ ክልል ባዘጋጀው የ5ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ ውስጥ ስለ አሁን ጊዜ ግስ ምንም ሳይቀየሩ እንደሚከተለው ቀርበዋል።

- ተማሪዋ ወደ ትምህርት ቤት እየሄደች ነው።
- ልጁ ልብሱን እያጠበ ነው (ደቡብ 5ኛ፣137)።

እነዚህ የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድርም ሆነ የደቡብ ክልል ትምህርት ቢሮዎች ባዘጋጁቸው የ5ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡት ምሳሌዎች ግን ቀጣይነት ያለው የአሁን ጊዜን እንጅ የአሁን ጊዜን አያሳዩም። በአማርኛ የአሁን ጊዜ ከትንቢት ጊዜ ጋር ተመሳሳይ ሲሆን አምዱም የፍፅምት ቅርፅ ሳይሆን የኢ-ፍፅምት ቅርፅ (ሰብር-) ዓይነት ያለው ነው።

"…በሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ የተሰመረባቸውን ግሶች ወደ አሁን ጊዜ ቀይሯቸው፡፡ "

ሀ. ተማሪዎች ከትምህርት ቤት በታክሲ ይመለሳሉ (አ/አ መስተዳድር 5ኛ፣133)፡፡

በዚህ ምሳሌ ውስጥ "ይመለሳሉ" የሚለው የግስ ቅርፅ በአሁን ጊዜ የቀረበ ሆኖ ሳለ ወደ አሁን ጊዜ ቀይሯቸው ተብሎ መቅረቡ ትክክል አይደለም፡፡

" የሚከተሉትን ዓ/ነገሮች የአሁን ጊዜ ወይም ሀላፊ ጊዜ በማለት ለይታችሁ ፃፉ፡፡"

እ.ኤ.አ. በ2019 በርካታ የሀገራችን ሴት አትሌቶች የሜዳሊያ ባለቤት ሆነዋል (ኦሮምያ ክልል 5ኛ፣132)፡፡

ከላይ እንደሚታየውና የኦሮምያ ክልል ትምህርት ቢሮ ባዘጋጀው የ5ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ገጽ-132 እንደቀረበው "….<u>ሆነዋል</u>" ተብሎ የቀረበው ዓረፍተ ነገር የግስ ቅርጽ የቅርብ ሀላፊ እንጅ የአሁን ጊዜን (…ይሆናሉ) ወይም የሀላፊ ጊዜን (…ሆኑ) የሚለውን አያመለክትም፡፡

" የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች በቅርብ ሀላፊ ቅርፅ ጻፋቸው፡፡"

ምሳሌ- ህፃኗ ጡት ጠባች፡፡ (የሩቅ ሀላፊ ጊዜ አመልካች ግስ/ቅርፅ)፡፡

- ህፃኗ ጡት ጠብታለች፡፡ (የቅርብ ሀላፊ ጊዜ አመልካች ግስ/ቅርፅ (አማራ ክልል 6ኛ፣100)፡፡

ከላይ እንደሚታየውና የአማራ ክልል ትምህርት ቢሮ ለ6ኛ ክፍል ባዘጋጀው የአማርኛ መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ ገጽ 100 "ህፃኗ ጡት ጠባች" በሚል የቀረበው ምሳሌ የሩቅ ሀላፊ ሳይሆን የዋህ ሃላፊ ነው፡፡ የሩቅ ሃላፊ ከሆነ "ህፃኗ ጡት ጠብታ ነበር" ተብሎ መቅረብ ነበረበት፡፡

" በሚከተሉት ጥያቄዎች ውስጥ ያሉትን የጊዜ ዓይነቶች ለይታችሁ በደብተራችሁ ፃፉ፡፡"

ምሳሌ፡- አክስቴ ወደ ሀገሯ ልትመለስ ነው፡፡ የወደፊት ጊዜ

አክስቴ ወደ ሀገሯ እየተመለሰች ነው፡፡ የአሁን ጊዜ

አክስቴ ወደ ሀገሯ ተመልሳለች፡፡ የሀላፊ ጊዜ (አ/አ መስተዳድር 5ኛ፣55)፡፡

ከላይ እንደሚታየውና የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር ትምህርት ቢሮ ለ5ኛ ክፍል ባዘጋጀው የአማርኛ መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ ገጽ 55 "አክስቴ ወደ ሀገሯ ተመልሳለች" በሚል የቀረበው ምሳሌ የሀላፊ ጊዜ ሳይሆን የቅርብ ሃላፊ ነው፡፡ የሀላፊ ጊዜ ከሆነ "አክስቴ ወደ ሀገሯ ተመለሰች" በሚል መቅረብ ነበረበት፡፡ በአማርኛ የአሁን ጊዜና የወደፊት ጊዜ ተመሳሳይ ቅርፅ ስላለው በተለያዩ የግስ ቅርፆች መቅረብ አልነበረበትም፡፡

"ቀጥለው የቀረቡትን ዓ/ነገሮች በምሳሌው መሰረት ነጠላ ወይም ውስብስብ ዓ/ነገር በማለት ለይታችሁ አሳዩ፡፡ "

ምሳሌ፡- አየር በአየር መነገድ ሐገርንና ወገንን ይጎዳል፡፡ ውስብስብ ዓ/ነገር ይላል (አ/አ መስተዳድር 6ኛ፣99)፡፡

ከላይ እንደሚታየውና የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር ትምህርት ቢሮ ለ6ኛ ክፍል ባዘጋጀው የአማርኛ መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ ገጽ 99 "አየር በአየር መነገድ ሐገርንና ወገንን ይጎዳል" በሚል የቀረበው ምሳሌ ነጠላ ዓ/ነገር እንጅ ውስብስብ ዓረፍተ ነገር አይደለም፡፡ ምክንያቱም "መነገድ" የሚለው ቃል "ግስ" ሳይሆን "አርዕስ (ስም)" ነውና፡፡ በተመሳሳይ የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር ለ6ኛ ክፍል ባዘጋጀው የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ገጽ 100 የሚከተለው ትዕዛዝና ምሳሌ ቀርቦ እናገኘዋለን፡፡

"ቀጥሎ በቀረቡት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ያሉትን ግሶች በምሳሌው መሰረት ለዩና በደብተራችሁ ፃፉ፡፡" ምሳሌ የጓሮ አትክልት በመሸጥ ቤታቸውን አሳመሩ፡፡ መልስ በመሸጥ፣አሳመሩ፡፡ (አ/አ መስተዳድር 6ኛ፣100)፡፡ ከዚህ ላይ "በመሸጥ" የሚለው አርዕስት የቃል ክፍሉ "ስም" ሆኖ ሳለ "ግስ" ተብሎ ነው የቀረበው፡፡

" በሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ያሉ ተዋቃሪዎችን ለይታችሁ አመልክቱ፡፡"

ምሳሌ፡- አልማዝ ትምህርት ቤት ሄደች፡፡

አልማዝ ባለቤት፣ ትምህርት ቤት ሄደች ማሰሪያ አንቀፅ ይላል (ኦሮምያ ክልል 6ኛ፣46)።

"…የዋህ ሀላፊ ማለት ድርጊቱ ተፈጽሞ ያበቃ ሆኖ የተፈፀመበትን የጊዜ ርቀት የማያመላክት ከሆነ የዋህ ወይም የቅርብ ሃላፊ ይባላል" ይላል።

ምሳሌ፡- ብርጭቆውን ሰበረች (ኦሮምያ ክልል 6ኛ፣75)።

ከላይ እንደሚታየውና የኦሮምያ ክልል ትምህርት ቢሮ ለ6ኛ ክፍል ባዘጋጀው የአማርኛ መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ ገጽ 46 ላይ እንደሚገኘው "ትምህርት ቤት ሄደች" የሚለው ግሳዊ ሀረግ ሙሉው ማሰሪያ አንቀጽ በሚል ተጠቅሷል። ገጽ 75 ላይ ደግሞ የዋህ ሀላፊ እና የቅርብ ሃላፊ ተመሳሳይ ቅርፅ እንዳላቸው ለማስረዳት "ብርጭቆውን ሰበረች" የሚለው ምሳሌ ቀርቦ እናገኘዋለን። ነገር ግን ሁለቱ የጊዜ አመልካች ግሶች ያላቸው ቅርፅ ተመሳሳይ አይደለም። ይኸውም ከላይ በምሳሌነት የቀረበው "…ሰበረች" የሚለው የዋህ ሃላፊ ሲሆን የቅርብ ሃላፊ ከሆነ ግን "….ሰብራለች" ተብሎ መቅረብ ነበረበት።

4. ማጠቃለያና አስተያየት

4.1. ማጠቃለያ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በአማራ ክልል፣ በኦሮምያ፣ በደቡብ ክልሎችና በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር ትምህርት ቢሮዎች ለ5ኛ እና ለ6ኛ ክፍል ባዘጋጇቸው የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የቀረቡትን የሰዋስው ጥያቄዎችና ምሳሌዎች ትክክለኛነት ከስነምዕላድ፣ ከቃል ክፍል፣ ከስነሀረግና ከዓረፍተ ነገር አንፃር መገምገም ነበር። በዚህ መሰረት የ5ኛ እና የ6ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት በዓላማ ተኮር የንሞና ዘዴ ከተመረጡ በኋላ በሰነድ ፍተሻ መረጃዎች ተሰብስበዋል። የተሰበሰቡት መረጃዎች በገላጭ የምርምር ዘዴ ተተንትነው የሚከተሉት ውጤቶች ተገኝተዋል።

በመጀመሪያ ደረጃ በሁለቱም የክፍል ደረጃዎች ለማየት የተሞከረው የምዕላድ አከፋፈልን የተመለከቱ ጥያቄዎችንና ምሳሌዎችን ነበር። በዚህ ንዑስ ርዕስ ሥር ነፃ ምዕላድንና ቅጥያዎችን በተመለከተ የቀረቡት ምሳሌዎችም ሆኑ ጥያቄዎች ሁሉም ከስህተት የጸዱ አልነበሩም። ለ5ኛ ለ6ኛ ክፍል ተማሪዎች ዋና ቃልንና ቅጥያዎችን ለማስተማር በቀዳሚነት የተመረጡት ግሶች ናቸው። የአማርኛ ግሶች ደግሞ መዋቅራዊ ውስብስብነት የሚታይባቸው ናቸው። ከግሶችም ደግሞ የጎረዱና ሥነልሳናዊ ሂደት የሚታይባቸውን ግሶች ቅጥያን ለማስተማር በቀዳሚነት መመረጣቸው የምዕላድ ጥያቄዎችም ሆኑ ምሳሌዎች ሰዋስዋዊ ትክክለኛነታቸውን በጠበቁ መንገድ እንዳይቀረቡ አድርጓቸዋል።

በሁለተኛ ደረጃ የሰዋስው ይዘቶችን ትክክለኛነት ለመገምገም የተሞከረው ከቃል ክፍል አንፃር ነበር። በዚህ መሰረት ለ5ኛ እና ለ6ኛ ክፍል ተማሪዎች የቃል ክፍልን በሚመለከት የቀረቡትን ጥያቄዎችና ምሳሌዎች ስንመረምር ከፍተኛውን ድርሻ የተሰጣቸው ተውሳከ ግስ ለሚባሉት የቃል ክፍሎች ነው። ይህ ደግሞ የመጻሕፍቱ አዘጋጆች ሁለተኛው ድክመታቸው ነው ማለት ይቻላል። ይኸውም በቋንቋው ውስጥ የሚገኙት ተውሳከ ግሶች በቁጥር ደረጃ ከሌሎች የቃል ክፍሎች አንፃር ሲነፃፀር እጅግ በጣም ጥቂት ሆኖ ሳለ ለ5ኛ እና ለ6ኛ ክፍል በተዘጋጁት የአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ መጻሕፍ ውስጥ ግን በተቃራኒው ከፍተኛ ድርሻ ተሰጥቷቸዋል። በዚህም የተነሳ የቃል ክፍላቸው ተውሳከ ግስ ያልሆኑ ቃላት ማለትም ስሞች፣መስተዋድዳዊ ሀረጎችና ጥገኛ ዓረፍተ ነገሮች ተውሳከ ግስ ተብለው ቀርበዋል። ይህ ደግሞ ተማሪዎች ስለተውሳከ ግስ ምንነትና አገልግሎት የተሳሳተ ግንዛቤ እንዲይዙ ያደርጋቸዋል።

በሶስተኛ ደረጃ ስለሰዋስዋዊ ይዘቶች ትክክለኛነት የተገመገመው ከሀረግ አንፃር ነበር። በዚህ መሰረት በ5ኛም ሆነ ለ6ኛ ክፍል በተዘጋጁት የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ ስለ ሀረግ ዓይነቶች የተሰጠው ትኩረት አነስተኛ ሲሆን ከመስተዋድዳዊ ሀረግ አንፃር የተሳሳተ ገለፃ ቀርቧል።

በመጨረሻም የሰዋስው ይዘቶችን ትክክለኛነት ለመገምገም የተሞከረው ከዓረፍተ ነገር አንጻር ነበር። በዚህ ንዑስ ክፍል ስር ስለ ዓረፍተ ነገር እና ስለ ባለቤት ምንነት የተሰጠው ገለፃም ሆነ ማብራሪያ ስህተት ያለበት ሲሆን በዋናነት የታየው ስህተት ግን ከጊዜ አመልካች የግስ ቅርፅ ጋር በተያያዘ ነበር። ይኸውም የአሁን ጊዜ፣ የትንቢት ጊዜ፣ የዋህ ሀላፊ፣ የቅርብ የሀላፊ ጊዜ እና የሩቅ የሃላፊ ጊዜ የሚሉት የግስ ቅርፆች በተለያዩ ክልሎች በተዘጋጁት የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የቀረቡት ገለፃዎችና ምሳሌዎች እርስ በእርስ የሚጣረሱና ትክክለኛነታቸውን የጠበቁ አይደሉም።

4.2. አስተያየት

1. ለወደፊት መማሪያ መጻሕፍት በሚዘጋጁበት ጊዜ ቅድሚያ የሙያው ቀረቤታ ያላቸው ሰዎች እንዲያዘጋጁት ቢደረግ፣

2. መማሪያ መጻሕፍት በተለይም በዝቅተኛ የክፍል ደረጃ ለሚገኙ ተማሪዎች በሚዘጋጁበት ጊዜ የብስለት ደረጃቸውን ታሳቢ ያደረጉ ምሳሌዎችንና ጥያቄዎችን ማቅረብ ቢቻል፣

3. በመጨረሻም መፃሕፍቱ ከመታተማቸው በፊት ባለሙያዎች አስተያየት እንዲሰጡበት ቢደረግ የተሻለ ነው፣

ዋቢ ጽሑፎች

ሀዋዝ ወልደየስ በየነ፣በሰና ጃጀው መኮንን፣ ነጅም ፈጅር መሐመድ እና ቻላቸው አንዳርጌ ተገኝ (2007) አማርኛ እንደአፍ መፍቻ ቋንቋ የተማሪ መጽሐፍ 5ኛ ክፍል፣ የኢፌዲሪ ትምህርት ሚኒስቴርና አብክመ ትምህርት ቢሮ።

መላኩ ጌቶ መኮንን፣ መስፍን ተካ በርሔ እና ውበቱ በዛብህ የሱፍ (2014) አማርኛ እንደ መጀመሪያ ቋንቋ የተማሪ መጽሐፍ 5ኛ ክፍል፣የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ።

አየለ መሎሬ፣ መስከረም አበራ እና ሰናይት ይልማ (2014) አማርኛ እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ የተማሪ መጽሐፍ 5ኛ ክፍል፣ የደቡብ ብ/ብ/ህ/ክ/መንግስት ትምህርት ቢሮ።

የኦሮሚያ ክልል ትምህርት ቢሮ (2014) አማርኛ እንደሁለተኛ ቋንቋ የተማሪ መጽሐፍ 5ኛ ክፍል።

የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ (2014) አማርኛ እንደአፍ መፍቻ ቋንቋ የተማሪ መጽሐፍ 6ኛ ክፍል።

የደቡብ ክልል ትምህርት ቢሮ (2014) አማርኛ እንደሁለተኛ ቋንቋ የተማሪ መጽሐፍ 6ኛ ክፍል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ (2014) አማርኛ እንደ መጀመሪያ ቋንቋ የተማሪ መጽሐፍ 6ኛ ክፍል።

የኦሮሚያ ክልል ትምህርት ቢሮ (2014) አማርኛ እንደሁለተኛ ቋንቋ የተማሪ መጽሐፍ 6ኛ ክፍል።

ማረው ዓለሙ (2003) ዘመናዊ የአማርኛ ማስተማሪያ ዘዴ። አዲስ አበባ፣ አልፋ ማተሚያ ድርጅት።

ባዬይማም (2000) የአማርኛ ሰዋስው (የተሻሻለ)። አዲስአበባ፣ ት.መ.መ.ድ

ጌታሁን አማረ (1990) ዘመናዊ የአማርኛ ሰዋስው በቀላል አቀራረብ። አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት።

Akmajian, Adrian (2004) Linguisticss: An Introduction to Language and Communication (5thed.) New Delhi: Prentice Hall of India Plc.

Bachman, L. (1990*). Fundamental Considerations in Language Testing.* Oxford: Oxford University Press.

Brown, H. Douglas. (1994) *Principles of Language Learning and Teaching (3rd Ed.)* New Jersey: Prentice Hall Regents.

Brown, H. Douglas (2007). *Principles of language teaching and learning (5th ed.)* USA: Long man.

Bygate, M., Tonkyn, A., & Williams, E. (1994). *Grammar and the Language Teacher.* London: Prentice-Hall.

Chomsky, N. (1957) Syntactic Structures. The Hague: Mounton Random House.

Coleman J. & Klapper J. (2005). *Effective Learning and Teaching in Modern Languages.* London and New York: Rutledge.

Corder, S. P. (1973) Introducing Applied Linguistics. London: Penguin Books.

Cunnings worth A. (1984), *Evaluating and Selecting EFL Teaching Materials.* London: Heinemann.

Decapua, Andrea (2008) *Grammar for Teachers. Aguide to American English for Native and non- Native Speakers.* New York: Springer.

Ellis, Rod (March, 2006). "Current Issues in the Teaching of Grammar.An SLA Perspective." TESOL QUARTERLY. Vol.40, No.1 NewZealand: University of Auckland.

Grant, Neville (1987). *Making the Most of Your Text Book.* London: Longman.

Harmer, J. (1987). *Teaching and Learning Grammar*. London: Longman.

Harmer J. (1991). *The Practice of English Language Teaching.* London and New York: Longman.

Juzek, Tom S. (2016) Acceptability Judgment Task and Grammatical Theory. Jesus College, Oxford.

Keck, Casey and Kim, Youjin (2014) Pedagogical Grammar. Philadelphia: John Benjamins Publishing Company.

Nunan, D. (1991). *Language Teaching Methodology*. London: Prentice Hall International.

Ur, P. (1991). A Course in Language Teaching: Practice & Theory. Cambridge: Cambridge University Press.

Widodo, Handoyopuji (May, 2006) "Approaches and Procedures for Teaching Grammar" *English Teaching: Practice and Critique.*Volume 5, Number 1. (pp. 122-141). Retrived from: http://education.waikato.ac.nz/research/files/etpc/2006v5n1nar1.pdf on15/14/2011.